Ministry of justice

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 16
ADDIS ABABA 11th February, 2011

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፱/፪ሺ፫ ዓ.ም

የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ...ገጽ ፭ሺ፯፻፲፯

CONTENTS

Proclamation No. 699/2010

Protection of Witnesses and Whistleblowers of Criminal Offences Proclamation ........Page 5717

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፱/፪ሺ፫

## ስለወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ የወጣ አዋጅ

የወንጀል ድርጊቶች ከተፈጸሙ በኋላ ፈጻሚዎቹ ተደብቀው እንዳይቀሩና ህግ ፊት ቀርበው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ የህብረተሰቡ ሰላማዊ ኑሮ የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ መስጠት በኅብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ስጋት ሊያስከትሉ የሚችሉ ወንጀሎችን በማጋለጥ ወንጀልን ለመከላከል የሚረዳ በመሆኑ፤

የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች በምስክርነታቸው ወይም በጠቋሚነታቸው ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከሚደርስባቸው አደጋና ጥቃት ለመከላከልና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የጥበቃ ሥርአቶችን በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፱/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 699/2010.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PROTECTION OF WITNESSES AND WHISTLEBLOWERS OF CRIMINAL OFFENCES

**WHEREAS,** it is essential to create conducive situations in order to ensure the safety and security of the public by having criminal offenders brought to justice and sustain the right penalty;

**WHEREAS,** providing protection for witnesses and whistleblowers of criminal offences play a significant role for the prevention of crime by uncovering crimes that may cause serious threat to the public;

**WHEREAS,** it is found necessary to legislate the protection systems that need to be put in place in order to protect witnesses and whistleblowers of criminal offense from direct or indirect danger and attack they may face as a consequence thereof and thereby to ensure their safety;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### GENERAL

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Protection of Witnesses and Whistleblowers of Criminal Offences Proclamation No.699/2010."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 8.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Ministry of justice



## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ጠቋሚ ወይም ምስክር" ማለት በወንጀል ምርመራ፣ በወንጀል ክስ ወይም በወንጀል ማጣራት ሒደት መረጃ ወይም ምስክርነት የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ ሰው ነው፤

፪/ "የጥበቃ ተጠቃሚ" ማለት ከሚኒስቴሩ ጋር የጥበቃ ስምምነት የተፈራረመ ምስክር፣ ጠቋሚ ወይም የምስክር ወይም የጠቋሚ ቤተሰብ አባል ነው፤

፫/ "የመኖሪያ ስፍራን መቀየር" ማለት የጥበቃ ተጠቃሚን ከመኖሪያ ስፍራው ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው ሚኒስቴሩ በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር በሚያዘጋጅለት ቦታ ማስፈርን ወይም የጥበቃ ተጠቃሚው ነጻነትን የሚያሳጣ ቅጣት በመፈጸም ላይ ከሆነ ቅጣቱን በመፈጸም ላይ ካለበት ቦታ ወደተዘጋጀለት ሌላ የቅጣት መፈጸሚያ ቦታ ማዛወርን የሚመለከት የጥበቃ እርምጃ ነው፤

፬/ "ማንነትን መቀየር" ማለት የጥበቃ ተጠቃሚን ግላዊ መረጃዎች በከፊል ወይም በሙሉ ከአዲስ ሁኔታ ጋር እንዲስማማ አድርጎ ማስተካከል ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ አካላዊ ገጽታን መቀየርን የሚጨምር የጥበቃ እርምጃ ነው፤

፭/ "የዓይነ ቁራኛ ጥበቃ" ማለት ለጥበቃ ተጠቃሚ ስውር ጥበቃ ማድረግንና የረጅም ርቀት የመገናኛ መሣሪያ በመጠቀም በመኖሪያ ቤቱ ላይ የሚደረግ ቴክኒካዊ ቁጥጥርና ቀረጻን የሚያካትት የጥበቃ እርምጃ ነው፤

፮/ "ማንነትንና ባለንብረትነትን መደበቅ" ማለት የጥበቃ ተጠቃሚን ግላዊና ንብረቱን የሚመለከቱ ሰነዶችን በጊዜያዊነት መፍጠርንና መጠቀምን የሚያካትት የጥበቃ እርምጃ ነው፤

፯/ "ቤተሰብ" ማለት የትዳር ጓደኛን፣ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባል ወይም እንደ ሚስት አብሮ የሚኖር ሰውን፣ ልጅን፣ ወላጅን፣ እህትና ወንድምን፣ የትዳር ጓደኛ ልጅን እና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባል ወይም እንደ ሚስት አብሮ የሚኖር ሰው ልጅን ያጠቃልላል፤

## 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "whistleblower or witness" means a person who has given or agrees to give information or has acted or agrees to act as a witness in the investigation or trial of an offence;

2/ "protected person" means a witness, a whistleblower or a family member of a witness or a whistleblower who has entered into a protection agreement with the Ministry;

3/ "relocation" means a type of protection measure that involves temporary or permanent resettling of a protected person by the Ministry in a place, within the country or overseas, other than his place of residence or if the protected person is undergoing a penalty entailing loss of liberty, the transfer of him to another penitentiary;

4/ "change of identity" means a type of protection measure that involves modifying and adjusting parts or entire personal data of a protected person to a new situation and may include plastic surgery where necessary;

5/ "surveillance protection" means a type of protection measure that includes the conduct of covert protection of a protected person and surveillance and technical recording, by long-distance communication means, of the premises in which he resides;

6/ "concealing identity and property ownership" means a type of protection measure that involves temporary creation and use of documents relating to the identity and property of a protected person;

7/ "family" includes the spouse or cohabitant, the children, parents, siblings and the children of the spouse or cohabitant of a person;

Ministry of justice



፰/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፍትህ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፱/ "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፤

፲/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፩/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴት ፆታን ያካትታል።

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚደረግ ጥበቃ ተፈጻሚ የሚሆነው በሕግ የተደነገገው የፅኑ እስራት መነሻ ከግምት ሳይገባ አስር ዓመትና ከዚያ በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ በሚችል የወንጀል ድርጊት ተጠርጣሪ ላይ የሚሰጥ ምስክርነትን ወይም ጥቆማን ወይም የሚካሄድ ምርመራን በሚመለከት ሆኖ:-

ሀ/ የወንጀል ድርጊቱ ያለምስክሩ ወይም ያለጠቋሚው ምስክርነት ወይም ጥቆማ በሌላ ማናቸውም መንገድ ሊረጋገጥ ወይም ሊደረ ስበት የማይችል ሲሆን፤ እና

ለ/ በምስክሩ፣ በጠቋሚው ወይም በምስ ክሩ ወይም በጠቋሚው ቤተሰብ ህይወት፣ አካላዊ ደህንነት፣ ነጻነት ወይም ንብረት ላይ ከባድ አደጋ ይደርሳል ተብሎ ሲታመን፤

ነው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገ ገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ እና ኮሚሽኑ የጥበቃ ተጠቃሚ ላልሆኑ ምስክሮችና ጠቋሚዎችም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /ቸ/፣ /ኀ/፣ /ኘ/፣ /አ/ እና /ዘ/ የተደነገጉትን የጥበቃ እርምጃዎች ሥራ ላይ ሊያውሉ ይችላሉ።

8/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Justice, respectively;

9/ "Commission" means the Federal Ethics and Anti-Corruption Commission;

10/ "person" means natural or legal person;

11/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

1/ The protection under this Proclamation shall be applicable with respect to testimony or information given or investigation undertaken on a suspect punishable with rigorous imprisonment for ten or more years or with death without having regard to the minimum period of rigorous imprisonment:

a) where the offence may not be revealed or established by another means otherwise than by the testimony of the witness or the information of the whistleblower ; and

b) where it is believed that a threat of serious danger exists to the life, physical security, freedom or property of the witness, the whistleblower or a family member of the witness or the whistleblower.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Ministry and the Commission may also extend the protections provided under sub-article (1), (l), (m), (o), (p) and (t) of Article 4 of this Proclamation to witnesses and whistleblowers who are not protected persons.

Ministry of justice



## ክፍል ሁለት
## የጥበቃ እርምጃዎች

### ፬. የጥበቃ እርምጃ ዓይነቶች

፩/ የሚከተሉት የጥበቃ እርምጃዎች እንደሁኔታው በተናጠል ወይም በጣምራ ለጥበቃ ተጠቃሚ ተፈጻሚ ሊደረጉ ይችላሉ፡-

ሀ/ የአካልና ንብረት ደህንነት ጥበቃ፤

ለ/ የመኖሪያ ስፍራ መቀየርን ጨምሮ ደህንነቱ የተጠበቀ የመኖሪያ ቦታ መስጠት፤

ሐ/ ማንነትንና ባለንብረትነትን መደበቅ፤

መ/ ማንነትን መቀየር፤

ሠ/ ለራስ መጠበቂያ የነፍስ ወከፍ መሳሪያ መስጠት፤

ረ/ መረጃ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት ያለመከሰስ፤

ሰ/ መረጃ በሚሰጥበት የወንጀል ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊትም ሆነ በኋላ ተከሳሽ በጥበቃ ተጠቃሚው መኖሪያ ወይም የሥራ ቦታ ወይም ትምህርት ቤት አካባቢ እንዳይደርስ ማገድ፤

ሸ/ የፍርድ ሂደት ተጀምሮ ምስክርነት እስከሚሰጥ ድረስ የምስክር ማንነት እንዳይገለጽ ማድረግ፤

ቀ/ ምስክርነት በዝግ ችሎት እንዲሰጥ ማድረግ፤

በ/ ምስክርነት በአካል ሳይታይ ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆኖ ወይም ማንነትን በመሸፈን እንዲሰጥ ማድረግ፤

ተ/ ማስረጃ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በሌላ የተለየ ዘዴ እንዲቀርብ ማድረግ፤

ቸ/ በሚስጥር መያዝ ያለበት ካልሆነ በስተቀር ለጠቋሚ ጥቆማ ባቀረበበት ጉዳይ ላይ ወቅታዊ መረጃና ምክር መስጠት፤

## PART TWO
## PROTECTION MEASURES

### 4. Types of Protection Measures

1/ The following protection measures may be employed for a protected person separately or in combination, as the case may be:

a) physical protection of person and property;

b) providing a secure residence including relocation;

c) concealing identity and ownership;

d) change of identity;

e) provision of self-defense weapon;

f) immunity from prosecution for an offence for which he renders information;

g) prohibiting an accused person from reaching the protected person's residence, work place or school before or after a final judgment is delivered on the crime for which information is given;

h) not to disclose the identity of a witness until the trial process begins and the witness testifies;

i) hearing testimony in camera;

j) hearing testimony behind screen or by disguising identity;

k) producing evidence by electronic devices or any other method;

l) unless it is deemed confidential, providing information regarding the progress of investigation on what has been whistle blown and advice to a whistleblower;

Ministry of justice



ኀ/ እንዲመሰክር ለተጠራ ምስክር የጉዞና የውሎ አበል መስጠት፤

ነ/ የጥበቃ እርምጃው የመኖሪያ ስፍራን ለውጥ ካስከተለ የጓዝ ማጓጓዣ ወጪን መሸፈን፤

ኘ/ በበቀል የተወሰደ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲታገድ ወይም እንዲሻር ማድረግ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ የማካካሻ እርምጃ መውሰድ፤

አ/ በበቀል እርምጃ ለደረሰ ጉዳት የህክምና አገልግሎት በመንግሥት ሆስፒታል በነጻ መስጠት፤

ከ/ በጥበቃ እርምጃው ምክንያት ለደረሰ ገቢ ማጣት ወይም በበቀል እርምጃ ለደረሰ የመሥራት ችሎታ ማጣት የመሠረታዊ ፍላጎት ማሟያ ወጪን መሸፈን፤

ኸ/ በጥበቃ ሥር እያለ ለደረሰ ሞት የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ መሸፈንና ለቤተሰብ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፤

ወ/ የጥበቃ ተጠቃሚው የሥራና የትምህርት ዕድል እንዲያገኝ መርዳት፤

ዘ/ ለምስክሩ ወይም ለጠቋሚው የምክር አገልግሎት መስጠት ወይም እንዲያገኝ ማድረግ።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ለጥበቃ ሲባል ለጥበቃ ተጠቃሚው የሌለው የሙያ ማረጋገጫ እንዳለው ተደርጎ አይሰጠውም።

## ፭. የጥበቃ እርምጃን ዓይነት ስለመወሰን

ለጥበቃ ተጠቃሚ የሚሰጠውን የጥበቃ እርምጃ ዓይነት ለመወሰን የሚከተሉት ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል:-

፩/ የጥበቃ ተጠቃሚው ሊደርስበት ይችላል ተብሎ የሚገመተው የአደጋ ሁኔታ፤

፪/ የጥበቃ ተጠቃሚው የወንጀል ሪከርድ ያለበት ከሆነ ሊሰጥ የታሰበው ጥበቃ ሕዝብን ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑ ወይም ያለመሆኑ፤

m) providing transport allowance and per diem to a witness summoned to testify;

n) covering relocation cost where the protection measure entails relocation;

o) suspension or revocation of retaliatory administrative measures or taking any other compensatory measure;

p) provision of medical treatment free of charge at government hospitals in case of injury sustained as a result of retaliatory measure;

q) covering costs of basic needs in case of incapacity to work as a result of retaliatory measure;

r) in case of death as a result of retaliatory measure, covering funeral expenses and provision of pecuniary subsidy to family;

s) assisting the protected person to secure job and education opportunity;

t) providing or causing the provision of counseling service to the witness or whistleblower.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, a protected person may not be issued with professional certificate that he does not rightly possess for the sake of protection.

## 5. Determining Types of Protection Measures

The following shall be taken into account in determining the type of protection measure to be provided to a protected person:

1/ nature of the imminent danger to which the protected person is exposed;

2/ where the protected person has a criminal record, whether or not the intended protection measure entails a risk to the public;

Ministry of justice



፫/ ሊሰጥ የታሰበው ጥበቃ በሌላ ሰው መብትና ህጋዊ ጥቅም ላይ የሚያስከትለው ጉዳት፤

፬/ የጥበቃ ተጠቃሚው የጤናና የኑሮ ሁኔታ፤

፭/ የጥበቃ ተጠቃሚው ሊሰጥ ከታሰበው ጥበቃ ጋር ራሱን ለማላመድ ያለው ብቃት፤

፮/ ለጥበቃው የሚወጣው ወጪ መጠን፤

፯/ የጥበቃ ተጠቃሚው ከሌሎች የጥበቃ ተጠቃሚዎች ጋር ያለው ግንኙነት፤

፰/ በጥበቃ ተጠቃሚው ላይ በሕግ መሠረት የተጣሉ ግዴታዎችና ገደቦች፤

፱/ በሚኒስቴሩ የሚወጡ አግባብነት ያላቸው ሌሎች መመዘኛዎች።

## ክፍል ሦስት

## የጥበቃ ማመልከቻና ስምምነት

### ፮. የጥበቃ ማመልከቻ

፩/ ለጥበቃ ተጠቃሚነት የሚቀርብ ማመልከቻ፦

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ መሠረት ጥበቃ ሊደረግለት በሚገባው ሰው፤ ወይም

ለ/ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባው ሰው መጠየቅ በማይችልበት ጊዜ እርሱን በመወከል በመርማሪው፣ በዐቃቤ ህግ ወይም በማንኛውም ጉዳዩ ያገባኛል በሚል ሰው፤

ሊቀርብ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለጥበቃ ተጠቃሚነት የሚቀርብ ማመልከቻ፦

ሀ/ ጥበቃ የሚደረግለትን ሰው ማንነትና አድራሻ የሚገልጹ መረጃዎችን፤

ለ/ ለጥበቃው ምክንያት ከሆነው ጥቆማ፣ ምስክርነት ወይም ምርመራ ጋር የተያያዘውን የወንጀል ድርጊት፤

ሐ/ ጥበቃ በሚደረግለት ሰው ላይ የተጋረጠው አደጋ፤

3/ the damage that the intended protection measure may cause to the rights and lawful benefits of another person;

4/ the health and living conditions of the protected person;

5/ competence of the protected person to adapt himself with the intended protection measure;

6/ cost to be incurred for the protection;

7/ the relationship of the protected person with other protected persons;

8/ obligations and limitations imposed on the protected person according to law, if any;

9/ other similar appropriate considerations provided by the Ministry.

## PART THREE

## APPLICATION FOR PROTECTION AND PROTECTION AGREEMENT

### 6. Application for Protection

1/ An application for protection may be made:

a) by a person eligible for protection under Article 3 of this Proclamation; or

b) where the eligible person is unable to apply, by investigator, a public prosecutor or any interested person on behalf of such person.

2/ An application for protection to be submitted in accordance with sub-article (1) of this Article shall consist of:

a) information on the identity and address of the eligible person;

b) the offense related to the whistle blowing, testimony or investigation that constitute the ground for protection;

c) the danger that may likely sustain against the eligible person;

Ministry of justice



መ/ የጥበቃ ተጠቃሚ ለመሆን ከማመልከቱ በፊት የቀረበበት የወንጀል ወይም የፍትሐ ብሔር ክስ፣ ዕዳ ወይም ከመብት የመሻር ፍርድ ካለ ይህንኑ፤ እና

ሠ/ ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚጠየቁ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን፤

መያዝ አለበት፡፡

## ፯. በጥበቃ ማመልከቻ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት የቀረበው ማመልከቻ በመርማሪው ወይም በዐቃቤ ህግ ባልሆነ ጊዜ ሚኒስቴሩ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የመርማሪውን ወይም የዐቃቤ ህጉን አስተያየት መጠየቅ አለበት፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ለጥበቃ ተጠቃሚነት በቀረበ ማመልከቻ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ድንጋጌዎች መሠረት በ፴ ቀን ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ በቀረበለት የጥበቃ ተጠቃሚነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በአመልካቹ ህይወት፣ አካላዊ ደህንነት ወይም ንብረት ላይ ከባድ አደጋ ይደርሳል ብሎ ካመነ የአስቸኳይ ጊዜ የጥበቃ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ የቀረበለትን የጥበቃ ተጠቃሚነት ጥያቄ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለጠያቂው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፰. የጥበቃ ስምምነት

፩/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ከፊደል ተራ /ሀ/ እስከ /መ/ ከተመለከቱት የጥበቃ ዓይነቶች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ለመስጠት ከወሰነ ከጥበቃው ተጠቃሚ ጋር የጥበቃ ስምምነት መፈራረም አለበት፡፡

፪/ የጥበቃ ተጠቃሚው አካለ መጠን ያላደረሰ ወይም በፍርድ የተከለከለ ሰው ከሆነ የጥበቃ ስምምነቱ ከወላጆቹ ወይም ከአሳዳሪው ጋር ይፈረማል፡፡

d) any criminal charge or civil case, debt or decision of court depriving rights, brought against him before his application for protection; and

e) any other appropriate information required by the Ministry.

## 7. Decision on Application for Protection

1/ Where an application for protection is submitted in accordance with Article 6 of this Proclamation by persons other than the investigator or public prosecutor, the Ministry, shall, solicit the opinion of investigator or public prosecutor before delivering decision.

2/ The Ministry shall, in accordance with the provisions of Article 3 of this Proclamation, decide on an application made for protection within 30 days from receipt of the application.

3/ The Ministry may take urgent protection measures where it believes that grave danger is likely to occur to the life, physical security or property of the applicant until decision is given on the application.

4/ Where the Ministry rejects the application for protection, it shall notify the applicant in writing by stating the reasons thereof.

## 8. Protection Agreement

1/ Where the Ministry decides to implement one or more of the protection measures specified under sub-article (1) from (a) to (d) of Article 4 of this Proclamation, it shall enter into protection agreement with the protected person.

2/ Where the protected person is a minor or a judicially interdicted person, the protection agreement shall be concluded with his parent or guardian.

Ministry of justice



፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት የተደረገ የጥበቃ ስምምነት የጥበቃ ተጠቃሚው አካለ መጠን ካደረሰ ወይም የህግ ችሎታውን መልሶ ካገኘ በኋላ የሚቀጥል ከሆነ ስምምነቱን የጥበቃ ተጠቃሚው ራሱ መፈረም አለበት።

፱. ልዩ የጥበቃ ስምምነት

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ቢኖርም የጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ፦

ሀ/ መረጃ ወይም ምስክርነት የሚሰጠው በወላጁ ወይም በአሳዳሪው ላይ ሲሆን፤

ለ/ ወላጅ ወይም አሳዳሪ የሌለው ሲሆን፤

ሐ/ አስፈላጊው ጥረት ተደርጎ ወላጁን ወይም አሳዳሪውን ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ፤ ወይም

መ/ ወላጁ ወይም አሳዳሪው በቂ ባልሆነ ምክንያት ፈቃዱን ሳይሰጥ ሲቀር ወይም በማናቸውም ምክንያት ፈቃዱን መስጠት ሳይችል ሲቀር፤

ሚኒስቴሩ ከልጁ ጋር ልዩ የጥበቃ ስምምነት ሊፈራረም ይችላል።

፪/ አካለ መጠን ካላደረሰ ልጅ ጋር የተደረገ ልዩ የጥበቃ ስምምነት ከተፈረመበት ዕለት ጀምሮ ባሉት አስር ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ጥያቄ፦

ሀ/ ጥበቃው አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት፤ እና

ለ/ አካለ መጠን ካላደረሰ ልጅ ጋር የተደረገውን ልዩ የጥበቃ ስምምነት፤

መያዝ አለበት።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት አካለ መጠን ያላደረሰው ልጅ ጥቅምና ደህንነት ይበልጥ ሊረጋገጥ የሚችልበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የጥበቃ ስምምነቱን መሻር፤ ማጽደቅ ወይም ማሻሻል ይችላል።

3/ Where a protection agreement entered into under sub-article (2) of this Article continues to operate after the cessation of the legal incapacity, the protected person shall conclude the agreement by himself.

9. Special Protection Agreement

1/ Notwithstanding sub-article (2) of Article 8 of this Proclamation, the Ministry may enter into a special protection agreement with a minor where:

a) the minor is giving information or testimony against his parent or guardian;

b) the minor has no parent or guardian;

c) his parent or guardian could not be found notwithstanding reasonable efforts to find them; or

d) his parent or guardian is unreasonably withholding his consent or unable to give his consent for any reason.

2/ A special protection agreement entered into with a minor shall be presented, for approval, to the Federal High Court within ten days from the date of signature.

3/ An application to be submitted to the Federal High Court under sub-article (2) of this Article shall contain:

a) the reasons justifying the protection; and

b) the special protection agreement entered into with the minor.

4/ The court to which an application is submitted under sub-article (2) of this Article may set aside, approve or amend the special protection agreement by taking into account the realization of the best interest and security of the minor.

Ministry of justice



፭/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፬/ መሠረት ልዩ የጥበቃ ስምምነቱን የሻረው እንደሆነ ሚኒስቴሩ አካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ ከጥበቃው ማሰናበት አለበት።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፬/ መሠረት የጸደቀ ወይም የተሻሻለ ልዩ የጥበቃ ስምምነት አስገዳጅ ስምምነት ይሆናል።

## ፲. የጥበቃ ስምምነት ሥራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ

የጥበቃ ስምምነት ሥራ ላይ የሚውለው በጥበቃ ተጠቃሚውና በሚኒስቴሩ መካከል ከተፈረመበት ዕለት ጀምሮ ይሆናል።

## ፲፩. የጥበቃ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች ግዴታዎች

፩/ የጥበቃ ተጠቃሚው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

ሀ/ ለጥበቃ ስምምነቱ ምክንያት ለሆነው ጉዳይ ምርመራ ወይም ክስ እውነተኛ፣ ግልጽና የተሟላ መረጃ ወይም ማስረጃ የመስጠት ወይም በፍርድ ቤት ምስክርነት የመስጠት፤

ለ/ ሚኒስቴሩ አዘጋጅቶ የሚያቀርበውን የግላዊ መረጃ መጠይቅ በትክክል የመሙላት፤

ሐ/ የጥበቃ እርምጃውን ከሚያደናቅፍ ተግባር የመቆጠብ፤

መ/ ጥበቃውን አስመልክቶ የተሰጡትን ትዕዛዞችና መመሪያዎች የመቀበልና ተግባራዊ የማድረግ፤

ሠ/ በሚኒስቴሩ ሲጠየቅ የህክምና ምርመራ በማድረግ ውጤቱን የማሳወቅ፤

ረ/ በሚኒስቴሩ ሲጠየቅ ከአደንዛዥ ዕፅ ወይም አልኮል ሱስ ጋር በተያያዘ ምክር የመቀበል ወይም ህክምና የማድረግና ውጤቱን የማሳወቅ፤

ሰ/ በጥበቃ ስር ባለበት ጊዜ የቀረበበትን የወንጀል ክስ ወይም ከመብት የመሻር የፍርድ ውሳኔ ካለ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፤

5/ If the special protection agreement is set aside in accordance with sub-article (4) of this Article, the Ministry shall discharge the minor from protection.

6/ A special agreement approved or amended in accordance with sub-article (4) of this Article shall constitute a binding agreement.

## 10. Entry into Force of Protection Agreement

A protection agreement shall come into force as of the date of signing between the protected person and the Ministry.

## 11. Obligations of Parties to the Protection Agreement

1/ A protected person shall have the obligation to:

a) provide true, clear and complete information or evidence or testimony for investigation or prosecution in relation to the case which is the subject matter of the protection agreement;

b) complete correctly the form prepared by the Ministry for the purpose of obtaining personal information;

c) refrain from activities that may obstruct the protection measure;

d) accept and implement orders and directives relating to the protection;

e) when requested by the Ministry, undergo medical examination and produce the result thereof;

f) when requested by the Ministry, receive counseling or undergo medical treatment in relation to narcotic drugs or alcohol addiction and produce the result thereof;

g) inform the Ministry any criminal charge brought against him or deprivation of rights while under protection, if any;

Ministry of justice



ሸ/ በጥበቃ እርምጃው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር አዲስ ሁኔታ ሲከሰት ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፤

ቀ/ በዓይነ ቁራኛ ለመጠበቅ የመስማማት፤

በ/ የመሠረታዊ ፍላጎት ማሟያ ወጪ ተጠቃሚ ከሆነ በኢኮኖሚ ራሱን ለመቻል ጥረት ማድረግ፤ እና

ተ/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ግዴታዎች የመፈጸም።

፪/ ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ/ የጥበቃ ተጠቃሚውን መብትና ነጻነት አስፈላጊ ከሆነው መጠን በላይ ያለመገደብ፤

ለ/ የጥበቃ እርምጃውን ሊያደናቅፉ ይችላሉ ተብለው የጥበቃ ተጠቃሚው ሊቆጠብባቸው የሚገቡ ተግባሮችን አስቀድሞ የማሳወቅ፤

ሐ/ ለጥበቃ ተጠቃሚው የሚሰጠውን የመሠረታዊ ፍላጎት ማሟያ ወጪ መጠንና የቆይታ ጊዜ የማሳወቅ፤

መ/ የጥበቃ ተጠቃሚ በጥበቃ ሥር ባለበት ጊዜ አስፈላጊውን የምክር አገልግሎት እንዲያገኝ የማድረግ፤ እና

ሠ/ በጥበቃ ስምምነቱ የተመለከቱ የጥበቃ እርምጃዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ የመውሰድ።

## ፲፪. የጥበቃ ስምምነት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

፩/ የጥበቃ ስምምነት በሚከተሉት ምክንያቶች ይቋረጣል፡-

ሀ/ በስምምነቱ የተመለከተው ስምምነቱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ፤

ለ/ የጥበቃ ተጠቃሚው ሲሞት፤

ሐ/ የጥበቃ ተጠቃሚው የስምምነቱ ተጠቃሚ መሆንን በፈቃዱ ሲተው፤

h) inform the Ministry immediately of a new occurrence that may affect the protection measure;

i) agree to be under surveillance protection;

j) strive to sustain himself economically; when the type of protection is provision of basic needs; and

k) carry out other obligations deemed necessary by the Ministry.

2/ The Ministry shall have the obligations to:

a) not to restrict the right and freedom of the protected person more than the extent deemed essential;

b) notify to the protected person in advance, to refrain from any activity that may obstruct the protection measure;

c) inform the amount of cost of basic needs to be provided to the protected person and its duration;

d) ensure that the protected person get the necessary counseling services while under protection; and

e) take all necessary measures to ensure the effectiveness of the protection measures under the protection agreement.

## 12. Termination of Protection Agreement

1/ A protection agreement shall be terminated:

a) upon the expiry of the validity period fixed in the agreement;

b) upon the death of the protected person;

c) where the protected person voluntarily renounce the agreement;

Ministry of justice



መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት የተፈጸመ ከሆነ ስምምነቱ እንዲቋረጥ በወላጅ ወይም በአሳዳሪ በጽሁፍ ጥያቄ ሲቀርብ፤

ሠ/ አካለ መጠን ያላደረሰ ወይም በፍርድ የተከለከለ ሰው የህግ ችሎታ ማጣቱ እንዳበቃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት የጥበቃ ስምምነቱ እንዲቀጥል ፈቃዱን ለመስጠት እምቢተኛ ሆኖ ሲገኝ፤

ረ/ በጥበቃ ስምምነቱ የተወሰነው ጊዜ ሳያበቃ ጥበቃውን አስፈላጊ ያደረገው ሁኔታ ሲወገድ፤

ሰ/ የጥበቃ ተጠቃሚው ባሕሪ የራሱን ወይም የሌሎች የጥበቃ ተጠቃሚዎችን የጥበቃ እርምጃ ውጤታማ እንዳይሆን የሚያደርግ ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

ሸ/ የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገጉትን ግዴታዎች ሲጥስ።

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /ረ/፣ /ሰ/ ወይም /ሸ/ መሠረት የጥበቃ ስምምነቱን ከማቋረጡ በፊት መቼና ለምን እንደሚቋረጥ በመግለጽ የጥበቃ ተጠቃሚው አስተያየቱን በጽሑፍ እንዲያቀርብ እድል መስጠት አለበት።

፫/ ሚኒስቴሩ የጥበቃ ተጠቃሚው የሰጠው አስተያየት ተቀባይነት ያለው ሆኖ ያገኘው እንደሆነ የጥበቃ ስምምነቱ እንዲቀጥል ይወስናል።

፬/ የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት እንዲያውቀው በተደረገ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መልስ ያልሰጠ እንደሆነ ወይም የሰጠው አስተያየት ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ወይም በአድራሻው ተፈልጎ ያልተገኘ እንደሆነ ሚኒስቴሩ የጥበቃ ስምምነቱ እንዲቋረጥ ይወስናል።

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የጥበቃ ስምምነት ሲቋረጥ ሚኒስቴሩ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ አለበት።

d) in the case of an agreement concluded under sub-article (2) of Article 8 of this Proclamation, where termination of the agreement is demanded, in writing, by the parent or guardian of the protected person;

e) where a minor or judicially interdicted person refuses, upon secession of his legal incapacity, to consent to the continuation of the agreement in accordance with sub-article (3) of Article 8 of this Proclamation;

f) where the circumstance that necessitated the protection ceases to exist prior to the expiry date of the agreement;

g) where the conduct of the protected person renders ineffective the protection measure of himself or the others; or

h) where the protected person violates his obligations under sub-article (1) of Article 11 of this Proclamation.

2/ The Ministry shall, before terminating a protection agreement in accordance with sub-article (1) (f), (g) or (h) of this Article, inform the protected person as to when and why the protection agreement is to terminate and give him the opportunity to present his opinion in writing.

3/ The Ministry shall decide the continuation of the protection agreement where it finds that the opinion given by the protected person is acceptable.

4/ The Ministry shall terminate the protection agreement where the protected person fails to respond within one month from receipt of notification under sub-article (2) of this Article or where the opinion he has submitted is not acceptable.

5/ Where protection agreement is terminated on the basis of this Article the Ministry shall notify same to the concerned organs.

Ministry of justice



## ፲፫. የጥበቃ ስምምነትን ስለማራዘም

፩/ የጥበቃ ተጠቃሚ የጥበቃ ስምምነቱ ለተጨማሪ ጊዜ እንዲራዘምለት ለሚኒስቴሩ ሊያመለክት ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ለጥበቃው ምክንያት የሆነው የአደጋ ስጋት ያልተወገደ መሆኑን ሲያምንበት ስምምነቱን ለተጨማሪ ጊዜ ያራዝማል።

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት የተደረገን ልዩ የጥበቃ ስምምነት ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በራሱ ተነሳሽነት እንዲራዘም ሊወስን ይችላል።

## ክፍል አራት
## ማንነትንና ባለንብረትነትን የመደበቅ እና ማንነትን የመቀየር የጥበቃ እርምጃዎች አፈጻጸም

## ፲፬. ማንነትንና ባለንብረትነትን የመደበቅ እርምጃ

፩/ የጥበቃ ተጠቃሚ ማንነቱንና ባለንብረትነትን ለመደበቅ የተሰጠውን ሰነድ ተጠቅሞ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ህጋዊ ግዴታ ውስጥ ለመግባት የሚችለው የሚኒስቴሩን ፈቃድ ሲያገኝ ነው።

፪/ የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለሚኒስቴሩ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ካላገኘ ሚኒስቴሩን በማሳወቅ በቀድሞ ስሙ ህጋዊ ግዴታ የሚገባለትን እንደራሴ ሊወክል ይችላል።

## ፲፭. ማንነትን የመቀየር እርምጃ

፩/ ሚኒስቴሩ ማንነትን የመቀየር የጥበቃ እርምጃ ሥራ ላይ እንዲውል የሚወስነው ሌሎች የጥበቃ እርምጃ ዓይነቶች የጥበቃ ተጠቃሚን ደህንነት ለመጠበቅ የማያስችሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው።

፪/ የጥበቃ ተጠቃሚው ማንነትን የመቀየር የጥበቃ እርምጃ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለሶስተኛ ወገኖች የገባቸውን ህጋዊ ግዴታዎች መፈጸም አለበት።

## 13. Extension of Protection Agreement

1/ A protected person may apply to the Ministry for the extension of a protection agreement for additional period.

2/ The Ministry shall, where it is convinced that the threat which necessitated the protection still exists, extend the protection agreement for additional period.

3/ The Ministry, on its own motion, may decide to extend special protection agreement entered pursuant to Article 9 of this Proclamation, when necessary.

## PART FOUR
## APPLICATION OF CONCEALING IDENTITY AND PROPERTY OWNERSHIP AND CHANGE OF IDENTITY

## 14. Concealing Identity and Property Ownership

1/ A protected person, whose identity and property ownership has been concealed, may enter into a legal obligation that may have an impact on third parties by using the document issued to him upon obtaining the consent of the Ministry.

2/ Where the request submitted to the Ministry in accordance with sub-article (1) of this Article is not accepted, the protected person may, upon notifying the Ministry, appoint an agent to enter into a legal obligation in his real name.

## 15. Change of Identity

1/ The Ministry shall decide to apply change of identity only where it ascertains that other types of protection measures are incapable of protecting the security of the protected person.

2/ The protected person shall discharge his legal obligations towards third parties before change of his identity becomes effective.

Ministry of justice



፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ የጥበቃ ተጠቃሚው ህጋዊ ግዴታውን ለመወጣት የማይችል መሆኑን ካረጋገጠ ራሱ ህጋዊ ግዴታውን በመፈጸም ማንነትን የመቀየር የጥበቃ እርምጃው በሥራ ላይ እንዲውል ሊፈቅድ ይችላል።

## ፲፮. ከማንነት መቀየር በኋላ ስለሚቀጥሉ መብቶችና ግዴታዎች

፩/ የጥበቃ ተጠቃሚው ከማንነት መቀየር በኋላ በሚቀጥሉ መብቶች ለመጠቀምና ግዴታዎችን ለመወጣት እንደራሴ ሊወክል ይችላል።

፪/ የጥበቃ ተጠቃሚው ማንነቱ ከመቀየሩ በፊት ያላወቀው ህጋዊ ግዴታ የነበረበት መሆኑን ሚኒስቴሩ ከተረዳ የጥበቃ ተጠቃሚው ግዴታውን እንዲፈጽም መጠየቅ አለበት።

፫/ የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት ግዴታውን መወጣት ያልቻለ ወይም ያልፈለገ እንደሆነ ሚኒስቴሩ እንደሁኔታው የጥበቃ ተጠቃሚውን ግዴታ ይፈጽማል ወይም የጥበቃ ስምምነቱ እንዲቋረጥ ያደርጋል።

## ፲፯. አዲስ የማንነት ሰነዶችን ስለመስጠት

፩/ ሚኒስቴሩ የማንነት መቀየርን የጥበቃ እርምጃ ሥራ ላይ እንዲውል ከወሰነ የጥበቃ ተጠቃሚውን የቀድሞና አዲስ ግላዊ መረጃዎች በተለይ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጁ መዛግብት አስፍሮ ይይዛል። የመዝገብ አጠባበቁም ባልተፈቀደላቸው ሰዎች ከቀድሞው መረጃዎች አዲሱን ወይም ከአዲሱ መረጃዎች የቀድሞውን የጥበቃ ተጠቃሚውን ማንነት ለመረዳት የማያስችል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፪/ የሰነድ ማስረጃ የሚሰጡ አካላት ሚኒስቴሩ የሚሰጣቸውን መረጃ መሠረት በማድረግ በአዲሱ ማንነት አግባብ ያላቸው ሰነዶችን የማዘጋጀትና ለጥበቃ ተጠቃሚው የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

## ፲፰. የጥበቃ ተጠቃሚው የግንኙነት መስመር

ማንኛውም ማንነቱ የተቀየረ ወይም ማንነቱና የባለንብረትነት መረጃው የተደበቀ የጥበቃ ተጠቃሚን መብትና ግዴታ የሚመለከት ግንኙነት በጥበቃ ተጠቃሚው ፈቃድ በሚኒስቴሩ አማካይነት ይፈጸማል።

3/ Notwithstanding sub-article (2) of this Article, the Ministry may, where it ascertains that the protected person is unable to discharge his obligations, allow the change of identity to become effective upon settling the obligations by itself.

## 16. Rights and Obligations Continuing After Change of Identity

1/ A protected person may appoint an agent to enjoy the rights and discharge obligations that may continue after change of identity.

2/ The Ministry shall require the protected person to discharge his obligation where it learns that he has a legal obligation that he is not aware of.

3/ Where the protected person is unable or unwilling to discharge his obligations under sub-article (2) of this Article, the Ministry may settle the obligations by itself or terminate the protection agreement, as the case may be.

## 17. Issuance of New Personal Documents

1/ The Ministry shall, where it decides to implement a protection measure involving the change of identity, enter the particulars of the original and the new identity of the protected person in records specifically designed for such purpose. It shall keep the records in such a way that unauthorized persons may not trace the original identity of the protected person from the new identity information or vice versa.

2/ Bodies competent to issue identification and other related documents shall have the duty to issue appropriate new documents to the protected person on the basis of information provided to them by the Ministry.

## 18. Communications of the Protected Person

Any communication regarding the rights and obligations of a protected person whose identity and property ownership has been changed or concealed shall be made through the Ministry with his consent.

Ministry of justice



## ፲፱. ቅድመ ጥበቃ የተፈጸመ ወንጀል

፩/ የጥበቃ ተጠቃሚ ከመሆኑ በፊት ወንጀል የፈጸመን የጥበቃ ተጠቃሚ ክርክሩን እንዲከታተል አግባብ ያለው ፍርድ ቤት ያዘዘ እንደሆነ ሚኒስቴሩ የጥበቃ ተጠቃሚውን ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት።

፪/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የቀረበን የጥበቃ ተጠቃሚ የጥበቃውን ዓላማ በማይጻረር ሁኔታ በክርክሩ እንዲሳተፍ ያደርጋል።

## ፳. ቅድመ ጥበቃ የተፈጸመ ወንጀል ምስክርነት

የጥበቃ ስምምነት ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በተፈጸመ የወንጀል ድርጊት እንዲመሰክር የተፈለገ የጥበቃ ተጠቃሚ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ የሚደርሰውና ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚመሰክረው በሚኒስቴሩ አማካይነት ይሆናል።

## ፳፩. በቀድሞ ማንነት የፍትሐ ብሔር ክርክር ስለማድረግ

፩/ የጥበቃ ተጠቃሚ በቀድሞ ማንነቱ የፍትሐ ብሔር ክርክር ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ በሚሰጠው ፈቃድና መመሪያ መሠረት በክርክሩ ሊሳተፍ ይችላል።

፪/ የጥበቃ ተጠቃሚው በቀድሞው ማንነቱ በፍትሐ ብሔር ክርክሩ እንዲሳተፍ ሚኒስቴሩ ያልፈቀደ እንደሆነ ክርክሩን በወኪሉ አማካይነት ሊያካሂድ ይችላል።

## ፳፪. የቀድሞ ማንነትን ስለመመለስ

፩/ ሚኒስቴሩ፡-

ሀ/ በጥበቃ ስምምነት የተመለከተው የጥበቃ ጊዜ ካበቃ ወይም የጥበቃ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት ማንነትን ከመቀየር በመለስ ባሉ ሌሎች የጥበቃ እርምጃዎች የጥበቃ ተጠቃሚውን ደህንነት ማረጋገጥ ይቻላል ብሎ ከወሰነ፤ እና

ለ/ የማንነት መቀየር እንደ ጋብቻና አባትነት ወይም እናትነት በመሳሰሉት በሶስተኛ ወገኖች አቋም ላይ ከፍ ያለ ተጽዕኖ የማያሳድር መሆኑን ካረጋገጠ፤

የጥበቃ ተጠቃሚው የቀድሞው ማንነቱ እንዲመለስ ያደርጋል።

## 19. Pre-Protection Offences

1/ Where court orders that a protected person attend a criminal trial for an offence he committed before the entitlement of protection, the Ministry shall produce him before the court.

2/ Where the protected person appears before it in accordance with sub-article(1) of this Article, the court shall conduct the proceeding in such a way that the participation of the protected person may not prejudice the purposes of the protection.

## 20. Pre-Protection Testimony

A protected person required to appear as a witness for criminal offence committed before the implementation of the protection agreement shall be served with summons and appear before court through the Ministry.

## 21. Civil Suit in Original Identity

1/ Where necessary, a protected person may take part in a civil proceeding in his original identity with the consent and directions of the Ministry.

2/ Where the Ministry disapproves the participation of a protected person in a civil proceeding in his original identity, the protected person may participate in the proceeding through his agent.

## 22. Restoration of Original Identity

1/ The Ministry shall decide to restore the original identity of a protected person:

a) where the time prescribed in the protection agreement expires or it believes, prior to the expiry of the agreement, that protection measures other than change of identity could ensure the security of the protected person; and

b) it ascertains that change of identity may not entail a major impact on the status of third parties such as marriage and paternity or maternity.

Ministry of justice



፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የቀድሞ ማንነት እንዲመለስ ከማድረጉ በፊት የጥበቃ ተጠቃሚው እንዲያውቀው በማድረግ አስተያየቱን እንዲሰጥበት ዕድል ይሰጠዋል።

፫/ የጥበቃ ተጠቃሚ የቀድሞው ማንነቱ ሲመለስ የአዲሱን የማንነት መታወቂያና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ሰነዶች ለሚኒስቴሩ መመለስ አለበት።

፬/ የጥበቃ ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት የአዲሱን የማንነት መታወቂያና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ሰነዶች እንደመለሰ ሚኒስቴሩ የቀድሞው ማንነት መታወቂያና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች በሚመለከታቸው አካላት እንዲሰጡ ያደርጋል።

፭/ የማንነት መታወቂያና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች የሚሰጡ አካላት ሚኒስቴሩ የሚሰጣቸውን መረጃ መሠረት በማድረግ የቀድሞውን ማንነት የሚመለከቱ ተፈላጊ ሰነዶችን ለጥበቃ ተጠቃሚው የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

፮/ የጥበቃ ተጠቃሚው በአዲሱ ማንነቱ ያደረጋቸው ሕጋዊ ግንኙነቶች ሕጋዊ ውጤቶች መጠበቃቸውን ሚኒስቴሩ ያረጋግጣል።

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፫. የፍትሕ አካላት ኃላፊነት

፩/ ጉዳዩ የሚመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ከፊደል ተራ /ሰ/ እስከ /ተ/ የተደነገጉት የጥበቃ እርምጃዎች እንደ አግባቡ መወሰዳቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል።

፪/ ጉዳዩ የሚመለከተው ዐቃቤ ሕግ፦

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /ለ/ የተመለከተውን የዐቃቤ ሕግ ተግባር የማከናወን ሃላፊነት እና

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ከፊደል ተራ /ሰ/ እስከ /ተ/ እንዲሁም በፊደል ተራ /ዘ/ የተደነገጉት የጥበቃ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል።

2/ The Ministry shall notify the protected person and give him the opportunity to forward his opinion before restoring his original identity pursuant to sub-article (1) of this Article.

3/ A protected person shall, upon restoration of his original identity, return the new personal identification and other related documents to the Ministry.

4/ The Ministry shall ensure that the protected person has been provided, by the concerned bodies, with personal identification and other related documents in his original identity upon return of his new personal identification and other related documents in accordance with sub-article (3) of this Article.

5/ Bodies competent to issue personal identification and other related documents shall have the duty to issue the required documents to the protected person in his original identity on the basis of information provided to them by the Ministry.

6/ The Ministry shall ascertain that the legal obligations of the protected person entered into in his new identity remain intact after restoration to the original identity.

## PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 23. Responsibilities of Organs of Justice

1/ The concerned court shall have the responsibility to ensure that protection measures provided in sub-article (1) from (g) to (k) of Article 4 of this Proclamation are taken as may be appropriate.

2/ The concerned prosecutor:

a) shall have the responsibility to carry out the functions of a prosecutor provided for under sub-article (1) (b) of Article 6 of this Proclamation; and

b) may apply to court for the enforcement of protection measures provided for under Article 4 sub article (1) from (g) to (k) and (t).

Ministry of justice



፫/ የሚመለከተው መርማሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /ለ/ የተመለከተውን የመርማሪ ተግባር የማከናወን ኃላፊነት ይኖርበታል።

፳፬. የሚስጥር አጠባበቅ

፩/ ከጥበቃ ተጠቃሚ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መዛግብትና መረጃዎች በጥብቅ ሚስጥርነት ተፈርጀው መጠበቅ አለባቸው።

፪/ በሚኒስቴሩ የበላይ አመራር ካልተፈቀደ በስተቀር ሥራው ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ውጭ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከቱትን መዛግብት መመልከት አይችልም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም የጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ ወይም የነበረ ሰው፡-

ሀ/ መረጃው እንዲገለጽ የተስማማ እንደሆነ፤

ለ/ መረጃውን አስቀድሞ የገለፀው እንደሆነ፤

ሐ/ የጥበቃ ተጠቃሚው አስር ዓመትና ከዚያ በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረ እንደሆነ የተጠረጠረበትን የወንጀል ድርጊት ለማጣራት፤ ወይም

መ/ በወንጀል ክስ ዳኝነት የሌላ ተጠርጣሪን ንፁህነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፤

ሚኒስቴሩ መረጃውን ሊገልጽ ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተራ ፊደል /ሐ/ ወይም /መ/ መሠረት የጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ ወይም የነበረ ሰው መረጃ ለመግለጽ፡-

ሀ/ የመረጃው መገለፅ የጥበቃ ተጠቃሚ በሆነው ወይም በነበረው ሰው ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ፤ እና

ለ/ የመረጃው መገለፅ በሌላ መንገድ ሊተካ አለመቻሉ፤

መገናዘብ አለበት።

3/ The concerned investigator shall have the responsibility to carry out the functions of an investigator provided for under sub-article (1) (b) of Article 6 of this Proclamation.

24. Confidentiality

1/ Records and information relating to a protected person shall be classified as strictly confidential and kept accordingly.

2/ Any person may not have access to the records referred to in sub-article (1) of this Article except with the authorization of the top leadership of the Ministry.

3/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, beneficiary of protection or former beneficiary of protection:

a) consents to the disclosure;

b) has already disclosed the information;

c) where disclosure of the information is necessary to investigate a criminal offense punishable with ten or more years of rigorous imprisonment or death; or

d) his testimony found necessary to prove the innocence of another suspect in the criminal case;

the Ministry may disclose the information.

4/ To disclose the information of beneficiary of protection or former beneficiary of protection on the basis of sub article (3) (c) or (d) of this Article the following shall have to be taken into consideration:

a) the impact of disclosure of information on beneficiary of protection or former beneficiary of protection; and

b) absence of alternatives other than disclosing the information.

Ministry of justice



፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት መረጃው የተገለጸለት ሰው መረጃውን ለተገለጸለት ዓላማ ብቻ ማዋል አለበት።

## ፳፭. ቅሬታ ስለማቅረብ

፩/ በሚመለከተው የሚኒስቴሩ ኃላፊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ለጥበቃ ተጠቃሚነት ያመለከተ ሰው ወይም የጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ ወይም የነበረ ሰው ቅሬታውን ውሳኔው በደረሰው በ፲፭ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል።

፪/ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ቅሬታ ሲቀርብለት በአስር ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት። የሚኒስትሩ ውሳኔ ለፍርድ ቤት አቤቱታ የማይቀርብበት የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።

## ፳፮. የምስክርነት ተአማኒነት

የምስክር በዚህ አዋጅ መሠረት የጥበቃ ተጠቃሚ መሆን የሚሰጠውን ምስክርነት ተአማኒነት ደረጃ ዝቅ ለማድረግ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ አይችልም።

## ፳፯. ከሌሎች አካላት ጋር ስለሚደረግ ስምምነት

፩/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ጥበቃን ሥራ ላይ ለማዋል ከሚመለከታቸው የፌዴራል ወይም የክልል አካላት ጋር ስምምነት ሊፈጽም ይችላል።

፪/ ለምስክሮችና ጠቋሚዎች ተገቢውን ጥበቃ ለመስጠት እንዲቻል መንግሥት የሁለትዮሽ ወይም የባለብዙ ወገን ዓለም ዓቀፍ ስምምነት ሊፈራረም ይችላል።

## ፳፰. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚኒስቴሩ ትብብር ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት።

5/ A person to whom information is disclosed in accordance with sub-article (3) of this Article shall use it only for the purpose for which it has been disclosed.

## 25. Submission of Grievance

1/ Any person who has applied for protection or a person who is or was under protection may submit to the Minister his grievance on a decision of the concerned officer of the Ministry within 15 days from receipt of the decision.

2/ The Minister shall decide on a grievance submitted in accordance with sub-article (1) of this Article within 10 consecutive working days. The decision of the Minister shall be final and may not be appealable to court.

## 26. Credibility of Testimony

The fact that a witness is entitled to protection in accordance with this Proclamation may not be invoked as a ground to diminish the credibility of his testimony.

## 27. Agreement with other Bodies

1/ The Ministry may conclude agreements with organs of federal or regional states for the implementation of protection granted pursuant to this Proclamation.

2/ The government may conclude bilateral or multilateral treaties in order to provide effective protection to witnesses and whistle blowers.

## 28. Duty to Cooperate

Every person shall have the duty to cooperate for the implementation of this Proclamation, when requested by the Ministry.

Ministry of justice



**29. Penalty**

1/ Any protected person who:

a) contravenes sub-article (1) (a) of Article 11 of this Proclamation shall be punishable with rigorous imprisonment not exceeding ten years. Where, however, in a criminal case, the accused person has been wrongly convicted or has incurred rigorous imprisonment of more than ten years in consequence of the witness's act, the witness may himself be sentenced to the punishment which he has caused to be wrongfully inflicted;

b) without good cause fails to return the new identification and other related documents in accordance with sub-article (3) of Article 22 of this Proclamation shall be punished with simple imprisonment up to three years or with fine up to Birr 10,000 or with both;

c) refuses to cooperate with the Ministry in accordance with Article 28 of this Proclamation shall be punishable with not less than six months simple imprisonment or with fine not exceeding Birr 10,000 or with both;

d) contravenes sub article (1) (c) of Article 11 of this Proclamation and perform activity that obstructs the protection shall be punishable with rigorous imprisonment not less than one year and not exceeding five years or with fine not less than Birr 50,000 and not exceeding Birr 500,000 or with both.

2/ Any person who violates other provisions of this Proclamation shall be punishable in accordance with the relevant provisions of the Criminal Code.

**30. Transitory Provision**

Any protection agreement concluded before the coming into force of this Proclamation shall, in so far as it is consistent with the provisions of this Proclamation, be deemed to have been entered into according to this Proclamation.

**፳፱. ቅጣት**

፩/ ማንኛውም የጥበቃ ተጠቃሚ፦

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /ሀ/ የተደነገገውን ከተላለፈ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል። ሆኖም በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በመስካሪው ድርጊት ምክንያት የጥፋተኛነት ውሳኔ ተላልፎበት እንደሆነ ወይም ከአሥር ዓመት ፅኑ እሥራት በላይ ተፈርዶበት እንደሆነ የተመሰከረበት ሰው በስህተት በተወሰነበት ቅጣት ልክ ሀሰተኛ መስካሪው ሊወሰንበት ይችላል፤

ለ/ በቂ ምክንያት ሳይኖረው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ /፫/ በተደነገገው መሠረት የአዲስ ማንነት መታወቂያና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ሰነዶች ካልመለሰ እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ወይም እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ መሠረት ሚኒስቴሩ የሚያቀርብለትን የትብብር ጥያቄ ለመፈጸም እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከብር ፲ሺ በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /ሐ/ የተደነገገውን በመተላለፍ ጥበቃውን የሚያደናቅፍ ተግባር የፈጸመ ማንኛውም የጥበቃ ተጠቃሚ ከአንድ ዓመት በማያንስ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ወይም ከብር ፶ሺ በማያንስ ከብር ፭፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፪/ የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

**፴. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተደረገ የጥበቃ ስምምነት ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተደረገ ይቆጠራል።

Ministry of justice



፴፩. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፴፪. **ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፴፫. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

31. **Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

32. **Inapplicable Laws**

No law or customary practice may, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

33. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of February, 2011**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**